# ኅብረተሰቡ ደረሰኞችን ጥሎ መሄድ እንደሌለበት ተጠቆመ

**በእስክንድር መርሐጽድቅ**

ኅብረተሰቡ ግዥ የፈፀመባቸውን ደረሰኞች ከተቀበለ በኋላ በንግድ ድርጅቱ ውስጥ ጥሎ መሔድ እንደማይገባው ማሳሰቢያ ተሰጠ።

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደርና ትግበራ ቡድን አስተባባሪ አቶ አንተነህ ታምራት አንዳንድ ግዥ የተፈፀመባቸውንና ደንበኞች ጥለዋቸው የሄዱትን ደረሰኞች በድጋሚ ለሌላ ተመሣሣይ ተጠቃሚ እየሰጡ ተገቢውን የመንግሥት ገቢ ወደራሳቸው በማስገባት ላይ መሆናቸው ከተገኙ ጥቆማዎች መታወቁን አስታውቀዋል።

ከዚህ ሌላ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እውቅና ከሰጣቸው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ውጪ ሽያጭ የሚያከናውኑ መኖራቸውን ለመረዳት መቻላቸውን ገልፀዋል።

ይህን ድርጊት የሚፈጽሙትን በቁጥጥር ሥር ለማዋል የባለሥልጣኑ ሠራተኞች በማንኛ ውም ቀንና ሰዓት ስውር ክትትል እያደረጉ መሆናቸውን አስታውቀው ድርጅቶቹ ከእንደዚህ ዓይነት ድርጊት እንዲቆጠቡ አሳስበዋል።

ተጠቃሚዎቹም በሱፐር ማርኬቶች፣ በምግብና መጠጥ ቤቶች፣ በሥጋ ቤቶችም ሆነ በሌሎች ድርጅቶች ከተጠቀሙ በኋላ ደረሰኝ እንዲጠይቁና ከተሰጣቸውም በኋላ የራሳቸው መሆኑን ደረሰኙ ላይ በተመዘገበው ቀንና ሰዓት በማረጋገጥ ይዘውት እንዲሄዱ አስገንዝበዋል። እንዲሁም ድርጅቶቹ በትክክለኛው ማሽን ስለመጠቀማቸው በደረሰኙ መጨረሻ ላይ ET የሚል ምልክት መኖሩን እንዲያረጋግጡ አመልክተዋል።